# ዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም የአቡነ ሙሴ ገዳም ታሪክ፣ ኪነ ሕንፃና ጥንታዊ ሥዕላት ጥናት[1]

ጸጋዬ እባበይ*

***Abstract***

*The main objective of this study is to canvass the historical and architectural aspect of Addis Amba Mädhané Aläm, one of the long forgotten rock cave churches of Mäqét. To accomplish this objective, field observation, interview and document analysis were employed as important instuments of data collection. The collected data were descrbed and explained qualitatively. The study showed that the church was established by Abunä Musé, also was known as Abunä Minas, probably the second bishop of Ethiopian Orthodox Church in the late 4th or early 5th centuries A.D. There are more than six caves excavated in to a soft rock. The main cave church of Madhane Alam, among others, is unique particualry due to its monolithic nave situated at the center of the cave. The appearance of the nave is uncommon in the rock cave church tradition of Ethiopia. The nave consists of the major architectural works of the cave, including cross shaped windows, rectangular doorways, flat pillars and dome. The old enough canopy, a large processional umbrella permanently attached on the roof of the chanting place is the other feature that made the cave different. It is uncommon local handcraft not found elsewhere. It is crafted locally by intertwining bark of a tree. It is also impressively painted and decorated. Regrettably, this old antiquity is seriously deteriorated. The cave also witnesses archaic mural paintings which are difficult to date. Apart from its architectural and historical values, the cave has its own spiritual significance. Therefore, its values should be recognized to increase the flow of believers and tourists. Continuous recording of its values should also be done.*

*ቍልፍ ቃላት፡- መቄት፣ ዐዲስ አምባ ታሪክ፣ ኪነ ሕንፃ፣ ጥንታዊ ሥዕላት*

[1] ይኽ ጥናት በማኅበረ ቅዱሳን ፯ኛው ዐመታዊ የጥናት ጉባኤ ላይ የቀረበ ሲኾን ከተሳታፊዎች የተሰጡ ጥቆማዎችንና አስተያየቶችን በማካተት ተሻሽሎ የቀረበ ነው።

*ዲያቆን ጸጋዬ እባበይ በዲላ ዩንቨርሲቲ በታሪክና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው።

# ፩. መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐለም ዐቀፋዊ ዕውቅና ያገኙትን የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ የበርካታ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት ናት፡፡ በላሊበላና በትግራይ አካባቢ የሚገኙት ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት በምሁራን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረትን ያገኙ ሲኾኑ፣ በሰሜን ወሎና በደቡብ ጎንደር በሚገኙ አካባቢዎችም ያልታዩ ጥንታውያን ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ በእነዚኽ አካባቢዎች በሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች ዙሪያ በምሁራን የተደረጉ ጥናቶች አለመኖራቸው ብቻ ሳይኾን በባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የተከናወኑ ተግባራትም እጅግ ውስን ናቸው፡፡ ምናልባት የሀገራችን የቅርስ አስተዳደርና እንክብካቤ አቋም ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የተሻለ መኾኑ ቢነገርም[2] በየቦታው ያልታወቁና እየወደሙ ያሉ ቅርሶችን ስንመለከት ደግሞ እንቅስቃሴው ወደ ኋላ እንደቀረና ሙያተኞችና እንክብካቤ የሚፈልጉ ቅርሶች ምን ያህል እንደተራራቁ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያኽል ጥንታዊው የናዙኝ ማርያም ሙሉ ወጥ ውቅር ቤተ ክርስቲያን ምንም ዕውቅና ስለሌለው ዛሬ ላይ ሕንፃው የከፋ አደጋ ደርሶበት እንደሚገኝ ከዚህ ቀደም ተገልጿል፡፡[3]

የዘርፉ ምሁራን እንዳስቀመጡት ያልታወቁ ቅርሶችን በየጊዜው በመከታተል ካልተመዘገቡ በስተቀር ለነገ የሚኾን የተሟላ የቅርስ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ይኾናል፡፡[4] አንዴ የወደሙ ቅርሶችን መመለስም አስቸጋሪ ስለኾነ ጥንታዊ ቅርሶችን መንከባከብ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከመንከባከብ ተለይቶ መታየት እንደሌለበት እሙን ነው፡፡[5] ያላቸው ታሪክና ፋይዳ እንዲታወቅ እንዲሁም እየደረሰባቸው ያለው ተግዳሮት በዳሠሣ ጥናት ተደግፎ መተግበር ያለበት ርምጃ ካልተወሰደ በጥንታዊ ቅርሶቹ ላይ እየደረሰ ያለውና ሊደርስ የሚችለው ችግር ቀጠሮ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ተከታታይ ምዝገባዎችንም ኾነ ጥናቶችን ለማካሔድ ምንም የመጓጓዣ አገልግሎት የሌለባቸው አስቸጋሪ ቦታዎችን መውጣትና መውረድ ይጠይቃል፡፡ በሽደሆ መቄትም ኾነ በሌሎች አጎራባች አካባቢዎች የሚገኙ ጥቂት የማይባሉ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ተመዝግበው የማይገኙት ለዚኽ ሳይኾን

[2]Finneran, N. T*he Archaeology of Ethiopia.* London: Routledge, 2007. p. 265

[3]Tsegaye Ebabey, A Survey of Rock Hewn Churches in Maqet Warada, North Wallo. Unpublished MA Thesis, Addis Ababa University, Department of Archaeology, 2014. p. 94. ጸጋዬ እባበይ የደብረ ገነት ናዙኝ ማርያምና የአቡነ አሮን መንክራዊ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክና ኪነ ሕንፃ ዳሠሣ ጥናት፡፡ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት*፡፡ ቊጥር ፬፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ዐዲስ አበባ፣ ፳፻፰፣ ገጽ ፻፴፩-፻፴፯፡፡

[4]Letellier, R. *Recording, Documentation, and Information Management for the Conservation of Heritage Places: Guding Principles.* Los Angelos: The Getty Conservation Institute, 2007. XV.

[5]Timothy, D. J. & Nyaupane, G. P. *Cultural Heritage and Tourism in Developing World: A Regional Perspective.* London & New York: Routledge, 2009. p. 20.

አይቀርም፡፡ በመቄት ወረዳ ካልተመዘገቡ አቡነ ሙሴ እንዳነፃቸው የሚነገሩ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ የዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም (የአቡነ ሙሴ) ገዳም ሲኾን ለኹለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በቀረበው ጥናት ተካቶ ያለ ነው፡፡ ከዚኽ ቀደም አቡነ ሙሴ ያነፁት የናዙኝ ማርያም ውቅር ቤተ ክርስቲያን ለአንባብያን የቀረበ ሲኾን ይኽ ጥናትም ሌላውን የአቡነ ሙሴ ሥራ የሚዳሥሥ ነው፡፡ ገዳሙ የቀደሙ አበው የኪነ ሕንፃ አሻራ ያረፈበትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ምንነት የተደጎሰበት ልዩ የታሪክ ማኅደር በመኾኑ ለታሪክ ወዳድ አንባብያንና ለኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ይደርስ ዘንድ በዚኽ ጥናት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ጽሑፉ የጥናቱን አካሔድ፣ የገዳሙን አካባቢያዊ መገኛና ገጽታ እንዲኹም ታሪኩን በዐጭሩ ካመላከተ በኋላ በዋሻው ውስጥ የሚገኙትን ዕሴቶች ማለትም ጥንታዊ የዕደ ጥበብ ውጤት (ድባብ)፣ ኪነ ሕንፃና የግድግዳ ላይ ሥዕላት በጥልቀት ለመዳሠሥ ይጥራል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊ ገለጻዎች በግርጌ ማስታወሻ ተቀምጠዋል፡፡

## ፩.፩ የጥናቱ ዳራ

በመግቢያው ላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ስለ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ቤተ ክርስቲያን ኪነ ሕንፃዊም ኾነ ሌሎች ጉዳዮችን ሊያሳዩ የሚችሉ ጥናታዊ ጽሑፎችን በነበረኝ ዳሠሥ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በውጭም ይኹን በሀገራችን ምሁራን ቤተ ክርስቲያኑን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ጥናቶች አለመኖራቸው እንደ ክፍተት ሊታይ ይችላል፡፡ የኹለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቴ ወደ ዐሥራ ዘጠኝ የሚደርሱ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናትን ቢያካትትም ስለ ዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ገዳም ሙሉ መረጃ ይዟል ማለት አይቻልም፡፡ ከዋሻው ውስጥ ከሚገኙት ድንቅ ጥንታዊ ሀብቶች አንጻር ሰፋ ባለ መልኩ በዚኽ ጥናት ለአንባብያን ማድረሱ ተገቢ ይኾናል፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው በሚገኙ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ገዳም በወረዳውም ኾነ በሌሎች የቅርስ ጥበቃ ባለሙያዎች የተከናወኑ ተከታታይ ምዝገባዎች አለመኖራቸው ሌላኛው ክፍተት ነው፡፡ ስለዚኽ የዚኽ ውቅር ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ኪነ ሕንፃዊ፣ ታሪካዊና መንፈሳዊ ሀብቶች በቅርስ ጥበቃ አካላት፣ በአጥኚዎችና ከቦታው ራቅ ብለው በሚገኙ ምእመናን ዘንድ የማይታወቁ ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ በዚኽ ጥናት የሚዳሠሡት ጉዳዮች የገዳሙ የምሥረታ ታሪክ፤ የዋሻው ውስጥ ጥንታዊ የዕደ ጥበብ ቅርስ፤ የዋሻው ኪነ ሕንፃዊ መገለጫዎችና የዋሻው ጥንታዊ የግድግዳ ላይ ሥዕላት ናቸው፡፡

## ፩.፪ የጥናቱ ዐላማዎች

### ፩.፪.፩ ዋና ዐላማ

**የጥናቱ ጠቅላላ ዐላማ የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳምን ታሪካዊ ዳራ፣ ጥንታዊ የዕደ ጥበብ ቅርስ፣ ኪነ ሕንፃና የግድግዳ ላይ ሥዕላት ማጥናት ነው፡፡**

### ፩.፪.፪ የጥማናቱ ንኡሳን ዐላማዎች

የቤተ ክርስቲያኑን ታሪክ መዳሠሥ፣ ዋሻው ውስጥ ስለሚገኘው ድንቅና ታሪካዊ ጥበበ ዕድ ውጤት (ድባብ) ትንተና መስጠት፣ የዋሻውን ኪነ ሕንፃዊ መገለጫና የግድግዳ ላይ ሥዕላት ላይ ገለጻ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡

## ፩.፫ የጥናቱ ወሰን

በመቄት ወረዳ ብቻ በአቡነ ሙሴ አማካኝነት እንደታነፁ የሚነገርላቸው ከ፲፬ የማያንሱ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡[6] ከእነዚህም ውስጥ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም ላይ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ታሪክ፣ በዋሻው ስለሚገኘው ጥንታዊ ድባብ፣ ኪነ ሕንፃና የግድግዳ ሥዕላት ላይ ያተኩራል፡፡

## ፩.፬ የጥናቱ ጠቀሜታ

ይኽ ጥናት በአካባቢው ጠለቅ ያለ የምርምር ሥራ ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎችና ማስተዋወቅ ለሚሹ የቅርስና መስሕብነት ባለሙያዎች ጠቃሚ መረጃ ሊኾናቸው ይችላል። በተለይም ብዙ ስላልተነገረላቸው አቡነ ሙሴ ማጥናት ለሚፈልጉ እንደመነሻ ሊጠቅማቸው እንደሚችል ይታሰባል፡፡

## ፩.፭ የጥናቱ ዘዴ

ኹሉም የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት የገዳሙን ሥርዐት በጠበቀ መልኩ ነው፡፡ መረጃዎቹ በቀጥታ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በሥዕለ ብርሃን መሣሪያና በጂፒኤስ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በገዳሙ የሚገኘው የገድለ አቡነ ሙሴ ቅጂ ሌላኛው የጥናቱ ዐቢይ መረጃ ነው፡፡ መረጃዎቹም በዐይነታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ ቀርበዋል፡፡

[6] Tsegaye 2014.

# ፪. የቤተ ክርስቲያኑ አካባቢያዊ ገጽታና የገዳሙ አመሠራረት ታሪክ

## ፪.፩ አከባቢያዊ ገጽታ

የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ[7] ውስጥ ይገኛል። ገዳሙ ከወረዳው ዋና ከተማ (ፍላቂት) በስተ ምሥራቅ በኩል ስምንት ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ከፍላቂት በቅርብ ርቀት ከምትገኘው ከገረገራ ከተማ በስተ ምሥራቅ በኩል የቻይናውን መንገድ ወደ ቀኝ በመተው ቢያንስ ለአንድ ሰዐት ተኩል ያህል በእግር ተጉዞ ቦታው ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ፫፳፻፷፯ ሜ. ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ ያለው ሲኾን በ0476140 ምሥራቅና በ1297278 ሰሜን (UTM Coordination) ይገኛል።


ገዳሙ ዐዲስ አምባ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በኹለት ገደላማ ተራሮች[8] መካከል የሚገኝ ሲኾን ለዐይን የሚማርክ አካባቢያዊ ገጽታ አለው። ከቤተ ክርስቲያኑ ለመድረስ ከዐዲስ አምባ ማርያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ አስቸጋሪ የኾነውን ቁልቁለት መውረድ ወይም ከሰንደጅ ማርያም በስተደቡብ በኩል ቁልቁል መውረድ ግድ ይላል፡፡ ዋሻው በግራኝ አሕመድ ወረራ ጉዳት እንዳልደረሰበት የሚነገር ቢኾንም በዘመነ አጸባ[9] ምክንያት ለብዙ ጊዜ ጠፍቶ ከቆየ በኋላ በይፋ በገዳምነት ተመሥርቶ አገልግሎት እስከሚሰጥ ድረስ በእነዚህ ተራሮች ተደብቆ የቆየ ነበር፡፡ አካባቢው አልፎ አልፎ ለአብነት በቆሙ ዕድሜ ጠገብ የወይራ፣ የጽድና የሌሎች ብዙ ዐይነት ዛፎች የተሸፈነ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ደቡብ ምዕራብ በኩል ከሸለቆው ዳር በፈዋሽነቱ የሚታወቀው የመድኃኔ ዐለም ጸበል ይገኛል፡፡ በደቡባዊ የቤተ ክርስቲያኑ አቅጣጫ በኩልም የመነኰሳት መኖሪያና

[7]መቄት ወረዳ ሸደሆ መቄት እየተባለም ይጠራል። ወረዳው ከ፲፬፻-፴፪፻ ሜ. ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ ያለው ሲኾን እጅግ ወጣ ገባ መልክአ ምድራዊ ገጽታ አለው። አካባቢው ከ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የጎንደር ነገሥታት መተላለፊያና ዋና የሃይማኖት ማእከል ነበረ፡፡ በአብነት ትምህርት ቤት የሚታወቀው መቄት በተለይም ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከጎንደር ነገሥታት ጊዜ ጀምሮ ለአካባቢው ዋና የሃይማኖት ማእከል የነበረና እስካሁንም ድረስ ከሚታወቁ የአብነት ትምህርት ቤቶች ማዕከል አንዱ ነው፡፡ ብዙ መምህራን ከዚህ ጉባኤ ፈልቀዋል፡፡ ለምሳሌ መምህር ቀጸላ ሠይፉ በኋላም የቀድሞ የጎንደር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ እንድርያስ ቀዳማዊ ተጠቃሽ ናቸው (አጽማቸው ያረፈው በዚሁ ደብር ነው)፡፡ ይኽ ትምህረት ቤት ታዋቂው መምህር ሠይፈ ሥላሴ ያስተማሩበት (ከ፲፱፻፷-፲፱፻፹፰ ድረስ) በመኾኑ እስከ ዛሬ ድረስም ጉባኤው ያለበት ቦታ የመምህር ሠይፈ ሥላሴ ቅጥር ግቢ በመባል ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ታዋቂው አለቃ ለማ ኃይሉ መቄት ከፈለቁት ሊቃውንት መካከል ነበሩ፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም ደብረ አቡነ አሮን በመቄት ከሚታወቁት የአብነት ትምህርት ቤቶች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡

[8] እነዚህ ገደላማ ተራሮች በመካከላቸው ሸለቆ የሚገኝ ሲኾን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ የሸደሆ መቄት ቆላማ አካባቢን ለመመልከት የሚያስችል ማዕዘን መሰል ክፍተትን ፈጥረዋል፡፡ በስተ ደቡብ በኩል የሚገኘው ተራራ ጫፍ ላይ ዐዲስ አምባ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስትገኝ በስተ ሰሜን በኩል ከሚገኘው ተራራ ጫፍ ላይ ደግሞ ሰንደጅ ማርያም ትገኛለች።

[9]ዘመነ አጸባ ወይም ክፉ ቀን ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት መቋረጥ ምክንያት እንደኾነ በአካባቢው ተደጋግሞ የሚነገር ነው። በተለያየ ጊዜ የወሎን አካባቢ ድርቅና ረሀብ ያጠቃው እንደነበር በታሪክ የሚታወስ ነው፡፡ ይኽ ዘመነ አጸባ ተብሎ በአካባቢው የሚጠቀሰው ግን ዐፄ ምኒልክ እንደነገሡ ለአምስት ተከታታይ ዐመታት ተከስቶ የነበረውን "ክፉ ቀን" ተብሎ የሚታወቀውን የሚያመለክት ነው፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን




ካርታ ፩. የውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ሥርጭት በመቄት ወረዳ



ሥዕለ ብርሃን ፪. የገዳሙ አካባቢያዊ ገጽታ-ከደቡብ በኩል በርቀት ሲታይ

## ፪.፪ የገዳሙ አመሠራረት

ተደጋግሞ እንደተገለጸው የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም የተመሠረተው በአቡነ ሙሴ በመኾኑ የጻድቁን ታሪክ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ስለታሪካቸው ከዚኽ ቀደም በጥቂቱ ለመግለጽ ተሞክሯል።[10] አቡነ ሙሴ በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት በመቄትና በሌሎችም አካባቢዎች በመዘዋወር እንዳስተማረና አያሌ አብያተ ክረስቲያናትን እንዳነፀ ገድለ አቡነ ሙሴ[11] ይገልጻል። በገድሉ ውስጥ በስም የተጠቀሱና ያልተጠቀሱ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ የዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ገዳም ከተጠቀሱት አንዱ ነው። በገድሉ መሠረት አቡነ ሙሴ ከተከበሩ ዮስጦስ (የዐረጋዊ ዮሴፍ ልጅ) እና ጽርስቅላ ወይም ሶሊያና ማርያም (የዶኪማስ ልጅ) የተወለደ ሲኾን እናትና አባቱ በዶኪማስ ቤት በተደረገው ሠርግ[12] ሙሽሮች የነበሩ ናቸው። ይኽ ሠርግም በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ ውኃው ወደ ወይን የተቀየረበት ነው። እንደተወለደም ቅዱስ ገብርኤል ሙሴ[13] ብሎ ሠይሞታል። ሕፃናት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ መኾናቸውን ካስተማረባቸው አንዱ አቡነ ሙሴ መኾኑንና በዚኽች ምድር ላይ ለአምስት መቶ ዐመታት ያኽል እንደቆየ ገድሉ ይገልጻል።[14] አቡነ ሙሴ እንደ አያቱ ዐረጋዊ ዮሴፍ ሐናፂ ነበር። በሐዋርያት ዘመን የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስትታነፅ አቡነ ሙሴ እንደነበርም እንዲኹ በገድሉ ላይ ተገልጾ ይገኛል።

ገድለ አቡነ ሙሴ ላይ የንግሥና ጊዜው ባይጠቀስም አቡነ ሙሴ አንስጣስዮስ ወይም ቴዎዶስዮስ ተብሎ በሮማ ግዛት ውስጥ በንግሥና ከቆየ በኋላ በግብፅ ሀገር በሚገኘው ገዳመ አስቄጥስ[15] በምንኵስና ተወስኖ ሳለ ለጵጵስና መመረጡ ይታወሳል። በንግሥና

[10]ጸጋየ እባበይ ፳፻፰ ዐ.ም.፣ ገጽ ፻፲፩-፻፲፫።

[11]ለዚኽ ጽሑፍ እንደማስረጃነት የተጠቀምኩት ገድለ አቡነ ሙሴ በገዳሙ የሚገኝ ቅጂ ነው። ገድሉ የአቡኑን ታሪክ ከልደቱ ጀምሮ የሠራውን ሃይማኖታዊና አስተዳደራዊ ሥራዎቹን ይገልጻል። በቅርብ ጊዜ የዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ገዳም መታሰቢያ በማለት ይኼው ቅጅ በግእዝና በዐማርኛ የታተመ ሲኾን ዕትሙን ለመመልከት ሞክሬያለሁ። በርካታ ግድፈቶች ያሉበት በመኾኑ እንደገና ሊታረምና ሊታተም የሚገባው ነው። ለምሳሌ ያኽል በግእዙ ተሠውረ የሚለው በዐማርኛ ዐረፈ ተብሎ ተተርጕሟል (ገድለ ብፁዓዊ አቡነ ሙሴ ካልዕ ሰላማ ሊቀ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ገጽ ፺፱ ተመልከት)። ይኽ ደግሞ የአቡኑን ታሪክ የሚያወዛግብ ያደርገዋል።

[12]ዮሐ. ፪፥፲፪።

[13]ሙሴ እስራኤልን ከፈርዖን አገዛዝ ነጻ አውጥቶ ባሕረ ኤርትራን በማሻገር ርስት ሀገራቸው ከነአንን እንዲወርሱ የመራ ነቢይ ሲኾን በሊቀ ነቢያት ሙሴ ታሪክ አንጻር አሕዛብን በወንጌል ብርሃንነት ከሞት ወደ ሕይወት የሚያሻግር መኾኑን ሲያበሥር ቅዱስ ገብርኤል ይኽን ስያሜ ለአባታችን እንደሰጣቸው የገዳሙ አባቶች ይገልጸሉ።

[14]ገድለ አቡነ ሙሴን (በገዳሙ የሚገኝ ቅጅ) ይመልከቱ።

[15]አስቄጥስ ከታላላቅ ጥንታዊ የግብጽ ገዳማት አንዱና የመጀመሪያው ነው። ገዳሙን የመሠረተው ታላቁ አባ መቃርስ ሲኾን የአባ መቃርስ ገዳም በመባልም ይታወቃል። ገዳሙ በዋድ ኤል ናትሩን የግብጽ በረሃማ አካባቢ በሚገኝ አስቄጥስ በታባለ ቦታ ስለሚገኝ ገዳመ አስቄጥስ ይባላል። ከዚኽ ገዳም በርካታ ቅዱሳን ተገኝተዋ *(Malatay, T.Y. Introduction to the Coptic Orthododx Church.* 1993, p. 60)።

ዘመኑ በሃይማኖት በመጽናት በግብጽም ኾነ በሌሎች የሮማ ግዛቶች እጅግ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አንጿል፡፡ ይኽ ታላቅ አባት በሀገራችን በጽጽስና ዘመኑ ያለው ታሪክ ብዙም የሚታወቅ አይደለም፡፡ የአቡነ ሰላማ ግን ታሪኩና ሕይወቱ ከሞላ ጎደል በብዙ ምሁራን ዘንድ መገለጹ እሙን ነው፡፡

አቡነ ሙሴ በትውልድ እስራኤላዊ ሲኾን ወደ ሀገራችን በማዕርገ ጵጵስና ተሹሞ የመጣው ደግሞ ከግብፅ መንበረ ማርቆስ ነው፡፡ ለጵጵስና የተሾመውም ምናልባት በዐራተኛው መ.ክ.ዘ. መጨረሻ አካባቢ ሳይኾን አይቀርም፡፡ በቅርብ ጊዜ ስለ ዲባ መቅደሰ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ በወጣ ኅትመት አቡነ ሙሴ አቡነ ሰላማን የተኩ መኾናቸውን ትውፊታዊ ምንጮች እንደሚያመለክቱ ተጠቁሟል፡፡[16] በአኵስም ምእመናን ዘንድ ዳግም ሰላማ ተብለው ይታወቁ ነበር፡፡[17] በገድሉ ላይ ተጠቅሶ ባይገኝም አባ ሚናስ የሚለው የሢመት ስሙ መኾኑ ቀደም ሲል ተመላክቷል፡፡[18] ኹለተኛው ጳጳስ ተብሎ ከአቡነ ሰላማ ቀጥሎ እንደነበረ በጸሓፍት የተጠቀሰው ሚናስ[19] ይኽ አቡነ ሙሴ የተባለው ነው፡፡ አቡነ ሙሴ በጵጵስና ዘመኑ በሀገራችን በርካታ ሕንፃዎችን በማነፅ በየጭራ[20] በኵል የኾጣ ወንዝን[21] ተሻግሮ ውብ አድርጉ ባነፃት የየድባ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሠውሯል የሚሉ አሉ፡፡[22] ዐዲስ አምባ የሚገኘው ገድላቸውም (በዐማርኛ ትርጒሙ የተፋለሰ ቢኾንም) በግእዙ እንደተሠወሩ ይገልጻል፡፡ በሌላ በኵል አቡኑ እንዳረፈና መቃብሩ የድባ ማርያም እንደሚገኝ የየድባ ገዳም አባቶች ይናገራሉ፡፡

ሙሴ የሚባል በአምስተኛው መ.ክ.ዘ አካባቢ የአዱሊስ (የአኵስም ግዛት ዋና ወደብ የነበረች) ጳጳስ እንደነበረ የተገለጸበት ኹኔታ አለ፡፡[23] ይኽ ጳጳስ እንዳረፈም

[16]Witakowsk, E. B. Yadba Maryam. In: *Encyclopedia Aethiopica.* Vol.5, Wies baden, Harrassowitz Verlag, 2014, p. 3.

[17]ገድለ አቡነ ሙሴ፣ ቅጠል ፻፶፡፡

[18]ጸጋየ ፳፻፫ ዐ.ም.፣ ገጽ ፻፲፬፡፡

[19]Sergew Hable Selassie *Ancient and Medieval Ethiopian Hisotry to* 1270. Addis Ababa: United Printers, 1972. p.110፤ *መርሻ አለኸኝ፣ ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፡፡* ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቊር ዐባይ ፕሪንተርስ፣ ፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፲፯፡፡

[20]የጭራ ዋድላ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ሲኾን አቡነ ሙሴ ከዐለት ዋሻ ቤተ ክርስቲያንን ያነፁበት ቦታ ነው፡፡ እርሱም የጭራ መድኃኔ ዐለም ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ይኽ ቤተ ክርስቲያን በጸሓፍት ዘንድ አይታወቅም፡፡ በዚኽ ወረዳ ውስጥም በአቡነ ሙሴ እንደታነፀ የሚነገርለት ዋሻ ሚካኤል ይገኛል (Witakowska, E.B. Washa Mika'el. In: Siegbert Uhlig (ed.), *Encyclopedia Aethiopica, Vol.4, 1150-1151::*

[21]የበሽሎ ወንዝ ገባር ነው፡፡

[22]መርቆርዮስ አረጋ፣ የቅዱሳን ታሪክ፣ ፫ኛ መጽሐፍ። ዐዲስ አበባ፡ አስግ ሉሲ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፹፰፣ ገጽ ፳፯፣፪፻፲፭።

[23]Sergew 1972: 110 Munro-Hay 1988, p. 114. ዳንኤል ክብረት፣ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፯፻፵፡፡

መረጃ አለ፡፡[24] የዐፄ ካሌብ ወንድም ሙሴ የሚባል መነኲሴም በስድስተኛው መ.ክ.ዘ መጀመሪያ አጋማሽ እንደነበርም ተገልጿል፡፡[25] ብዙ ድርሰቶችን የጻፈ መኾኑ የሚገመት ሚናስ የተባለ በ፮ኛው ምእት ዐመት የአኲስም ጳጳስም ነበር፡፡[26] ይኽ ኹሉ የስም ተመሳሳይነት ቢኾን እንጅ አቡነ ሙሴን ወይም ዳግም ሰላማ የተባሉትን አባ ሚናስን አለመኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሥርግው[27] እንደገለጸው የአምስተኛው መ.ክ.ዘ. የኢትዮጵያ ክርስትና ኹኔታ ግልጽ ኾኖ አልታወቀም፡፡ የአቡነ ሙሴ ታሪክ በውል አለመታወቁም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አቡነ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት መኾኑን ገድላቸው ይገልጻል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ሊደርሱ የሚችሉት በዐራተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ይመስላል፡፡ አብርሃ ከአጽብሐ ቀደም ብሎ በ፫፻፶ዎቹ ዐ.ም አካባቢ ሳያርፍ አይቀርም፡፡ ስለዚህ በትረ መንግሥቱ በአጽብሀ እየተመራ ቆይቷል ማለት ነው፡፡ አቡነ ሙሴ የመጡት አብርሃ ካረፈ በኋላ የመንግሥቱ አስተዳደር በአጽብሐ ወይም እነርሱን በተካቸው መሪ እየተመራ በነበረበት ጊዜ ሊኾን ይችላል፡፡ ገድላቸው ጊዜውን ከአብርሃና ከአጽብሐ ዘመነ መንግሥት አገናኝቶ መጥቀሱ ለዚህ ሳይኾን አይቀርም፡፡ በጥቅሉ አቡነ ሙሴ ሚናስ ወይም ዳግም ሰላማ በመባል ይታወቁ ነበር፡፡




*ሥዕለ ብርሃን ፫. የአቡነ ሙሴ ሥዕል (የድባ ማርያም ግድግዳ ላይ ከተሣለ ሥዕል የተወሰደ)*

[24] Sergew 1972, p.110

[25] Fiaccadori, G. Muse. *Encyclopedia Aethiopica. Vol.* 3. Wiesbaden, Harrassowitz Verlag, 2007), pp.1081-1082.

[26] *ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ ዐማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፡፡ ቊጥር ፪፣ ፲፱፻፷፱፡፡*

[27] Sergew 1972: PP. 109-110.

ከአቡነ ሙሴ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት መካከል በ፲፬ኛው መ.ክ.ዘ. አቡነ አሮን ከተሰደዱበት አዋሽ ወደ ደብረ ቀጢን ሲመለሱ በዳውንት አድርገው እንደመጡና ዲባ (ድባ) መቅደሰ ማርያምን እንደባረኳት በገድለ አቡነ አሮን[28] ላይ ተገልጿል፡፡ በገድለ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ[29] ላይም አባ ኪራኮስ የሚባል መምህር የሚኖርባት የጻድቁ ሙሴ ደብር እንደኾነች ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ይኽም የሚያሳየው የክርስትና ትምህርት በአቡነ ሙሴ አማካኝነት ከ፲፬ኛው መ.ክ.ዘ. እጅግ ቀደም ብሎ ወደ አካባቢው እንደ ደረሰና በርካታ አብያተ ክርስቲያናትም ቀደም ብለው እንደታነፁ ያስረዳል፡፡

በገድለ አቡነ ሙሴ ስለ ዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ገዳም እንደሚከተለው ተጽፎ እናገኛለን፡፡

> *ወእምዝ እንዘ ያንሶሱ እምሀገር ለሀገር በጽሐ ኀበ ምድረ አምባ ውኃ ዘትሰመይ ዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ወበህየ ገብረ ብዙኀ ተአምረ፤ ወሐነፀ ቤተ ክርስቲያን በዕብን ውቁር በስሙ ለመድኃኒነ፤ ወዘሐነፀ ካልአን ኢተከሥቱ እስከ ይእዜ፡፡*[30]
> [በዚያም ከሀገር ለሀገር ሲመላለስ አምባ ውኃ ምድር ዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ከተባለች ቦታ ደረሰ፡፡ በዚኽም ብዙ ተአምራትን አደረገ፡፡ በጌታችን ስም ከድንጋይ የተጠረበ ቤተ ክርስቲያንም ሠራ፡፡ ሌሎችንም እስካሁን ድረስ ያልተገለፁ አነፀ፡፡]

ከገድሉ በተጠቀሰው ሐሳብ ላይ የሚያወያዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ አምባ ውኃ ተብሎ የተጠቀሰው የቦታ ስምና መገኛ ትክክለኛነት በእርግጠኝነት ይኽ ነው ብሎ ለማለፍ የሚያስችል ነገር አላገኘሁም፡፡ ዛሬ ይኽን ስያሜ የያዘ የቦታ ስም በአካባቢው ማግኘት አልተቻለም፡፡ ዐዲስ አምባ ደግሞ በዚኽ ቦታ ውስጥ እንደሚጠቃለል ገድሉ ይጠቁማል፡፡ ዐዲስ አምባ ውኃ የሚለው ዛሬ ባይታወስም ቤተ ክርስቲያኑ ያለበት አካባቢ እስከዛሬ ድረስም ዐዲስ አምባ በመባል ይታወቃል፡፡ በመኾኑም በፊት ዐዲስ አምባ ውኃ የሚባለው ዛሬ በተለያዩ ስያሜዎች የሚታወቁትን ቦታዎች ሊያካልል ይችላል፡፡ ስያሜው በሒደት ዐዲስ አምባ በሚለው የጸና ሳይኾን አይቀርም፡፡

ሌላው “ … እስከ ዛሬ ድረስ ያልተገለጹ … ” የሚለው ተሠውረው ያሉ፤ እስከ ዛሬ ድረስ አገልግሎት ሰጥተው የማያውቁ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት በዚህ አካባቢ መኖራቸውን ስለሚያሳይ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው፡፡ “… እስከ ዛሬ ድረስ …” ሲል እስከ መቸ እንደኾነ ግልጽ አይደለም፡፡ ገድሉ የተጻፈበትን ጊዜ ለመውሰድ ብናስብም ገድሉ መቸ እንደተጻፈ ግልጽ የኾነ ነገር የለም፡፡ ገድሉ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ከተጠና መፍትሔ ሊኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን ገድሉ የተጻፈበት ጊዜ ቢታወቅም ቅሉ ከዚያ በኋላ የተገለጹ ስለመኖራቸው ሌላ ጥያቄ ነው፡፡ በአቡነ ሙሴ እንደታነፁ በትውፊት ብቻ

[28]ገድለ አቡነ አሮን፣ ቅጠል ፹፪ (አቡነ አሮን ገዳም የሚገኝ ያልታተመ የብራና መጽሐፍ)፡፡
[29]ገድለ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ዐዲስ አበባ፣ ዐዲስ ማተሚያ ቤት፣ ፳፻፬ ዐ.ም.፣ ገጽ ፰፡፡
[30]ገድለ አቡነ ሙሴ፡ ቅጠል ፻፶፩፡፡

የሚነገርላቸው ነገር ግን በአቡነ ሙሴ ገድል ያልተጠቀሱ ከዐዲስ አምባ ገዳም በተወሰነ ርቀት የሚገኙ አሉ። እነዚህም ዳስንጃ መድኃኔ ዐለም[31]፣ ዋሻ ሚካኤል[32] (ከዐዲስ አምባ በስተምዕራብ)፣ ጠምበቆት መድኃኔ ዐለም[33]ና አቃት ማርቆስ[34] (በስተምሥራቅ) ናቸው። በገድሉ ሌሎች አምስት ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት በተለያየ ርቀት ላይ ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ጠፍተው የተገኙ ናቸው።

ስለእነዚኽ አብያተ ክርስቲያናት ኹለት ዐይነት አከራካሪ ጉዳዮች ሊነሡ ይችላሉ። የመጀመሪያው ሐሳብ ለብዙ ዘመናት ከቆዩ በኋላ ስለመገኘታቸው ሲኾን ሌላኛው ደግሞ በአቡነ ሙሴ እንደታነፁ በአካባቢው ዘንድ ቢነገሩም በገድለ አቡነ ሙሴ ተጠቅሰው አለመገኘታቸው ነው። እነዚኽ ዋሻዎች በአካባቢው ትውፊታዊ ምንጭ መሠረት አገልግሎታቸው በአህመድ ግራኝ ወረራ ምክንያት ተቋርጦ ለብዙ ዘመናት ጠፍተው የቆዩና በቅርብ ጊዜ ተገኝተው ለአገልግሎት ክፍት የኾኑ ናቸው። እነዚኽ ሊኾኑ ይችላሉ ብሎ ለመናገር በግራኝ አሕመድ ወረራ ምክንያት ጠፍተው የቀሩ እንደነበሩ ይነገራል። እነዚኽ ወደ አገልግሎት የተመለሱ ቢኾኑም እስካሁንም ድረስ በዚኹ ምክንያት ጠፍተው የቀሩ በሌሎች አካባቢዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመቱ ቀላል ነው። ለምሳሌ ጋይንት ከተማ አካባቢ በ፳፻፯ ዐ.ም የተመለከትኩት እስካኹንም ድረስ ጠፍ ኾኖ የሚገኘው ውቅር ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሽ ነው።

[31]ዳስንጃ መድኃኔ ዐለም ከፍላቂት ከተማ በስተ ደቡብ ወይም ከእመሙዝ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በስተ ደቡብ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ውቅር ቤተ ክርስቲያን ነው። ይኽ ዋሻ ለብዙ ዘመናት ጠፍ ኾኖ ቆይቶ በ፲፱፻፸፰ ዐ.ም. አባ ኀሩይ በተባለ መነኵሴ አማካኝነት እንደገና ሊመሠረት ችሏል። ከአንድ አነስተኛ ቋጥኝ የታነፀ ሲኾን ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስ አለው (Tsegaye 2014, pp. 50-52)።

[32]ዋሻ ሚካኤል ከእመምዑዝ ገዳም በስተ ምሥራቅ በኩል በቅርብ ርቀት ይገኛል። ከአንድ ዐለታማ ኮረብታ ላይ የታነፀ ሲኾን ኹለት የዋሻ አብያተ ክርስቲያናትን ይዟል። የመጀመሪያው የዋሻው ክፍል የቅዱስ ሚካኤል ቤተ መቅደስ ነው። በውስጡ ወደ ስድስት የሚደርሱ ክፍሎች አሉት። ከዐራተኛው እስከ ስድስተኛው ያሉት ክፍሎች የመቅደሱ አካል ናቸው።ኹለተኛው የዋሻው ክፍል ደግሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ መቅደስ ነው። የዚኽ ዋሻ የቅኔ ማኅሌቱና የቅድስቱ ክፍሎች በተፈጥሮ አደጋ የወደሙ ሲኾን የቤተ መቅደሱ ኹለት ክፍሎች ግን ሕያው ኾነው ይገኛሉ። በመቅደሱ ውስጥም ግዙፍ የኾነ ከዐለት የታነፀ መንበር አለው (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፵፮-፶)።

[33]ጠምበቆት መድኃኔ ዐለም ከፍላቂት ከተማ በስተ ምሥራቅ በኩል አቃት ከተባለች አነስተኛ ከተማ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሲሔዱ ከገደላማ አካባቢ ሥር የሚገኝ ነው። ይኽ ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ለየት የሚያደርገው ለብዙ ዘመናት ተዳፍኖ ሳይታይ መቆየቱ ነው። የተገኘውም በአካባቢው እረኞች አማካኝነት በ፲፱፻፸፫ ዐ.ም ነው። በውስጡም የተለያዩ ንዋያተ ቅዱሳት የተገኙ ሲኾን ጥንት ቤተ ክርስቲያን መኾኑን ተረድቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የጌታችን የመድኃኔ ዐለም ጽላት እንዲገባ ተደርጓል (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፶፯-፶፱)።

[34]የአቃት ማርቆስ ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ከጠምበቆት መድኃኔ ዐለም በግምት የኹለት መቶ ሜትር ያኽል ርቀት አለው። ለብዙ ዘመናት የአካባቢው ሰዎች እንስሳትን ያረቡበት ነበር። ዋሻው ኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ሲኖሩት አሠራሩ ሥርዐተ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን የተከተለ አይደለም። ቤተ መቅደሱ የሚገኘው በስተምዕራብ በኩል መኾኑ ይኽን ያጎላዋል። ጥልቅ የኾነ የውኃ ጉድጓድ ከዋሻው ውስጥ ይገኛል (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፶፱-፷)።

ጠምበቆት መድኃኔ ዐለምን ስንመለከት በትክክል ከአህመድ ግራኝ ወረራ በፊት አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር የሚያስረዱ የተለያዩ ንዋያተ ቅዱሳት ተገኝተዋል፡፡ ዋሻው የተገኘው ተዳፍኖ ለብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ በመኾኑ ተሠውሮ የቆየ ነበር ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን የእነዚኽ ማስረጃዎች መገኘት ታንፀው በሥውር ከቀሩት መካከል እንዳልኾነ ይገልጹልናል፡፡ የሌሎቹ ግኝት ግን እንደጠምበቆት ውቅር ዋሻ ሕንፃ መሬት ውስጥ ተዳፍነው ሳይኾን በአካባቢው ያሉት ሰዎች በፊት ጊዜም የሚያውቋቸውና ጥንት ቤተ ክርስቲያን እንደነበሩ በመረዳት በቅርብ ጊዜ ለአገልግሎት የከፈቷቸው ናቸው፡፡ ይኽ ደግሞ እንደመገለጽ አይቆጠርም፡፡ በሥውር ሲል የሰው ዐይን ያላያቸው ጊዜው ሲደርስ ብቻ የሚገለጹ ወይም ለዕይታ የሚበቁ ማለት ነው፡፡ ስለዚኽ ይኽ ጉዳይ እጅግ አከራካሪ ኾኖ እናገኘዋለን፡፡ በአንድ በኩል የአካባቢው አፈ ታሪክ እነዚኽን ቅርብ ጊዜ የተገኙ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት በአቡነ ሙሴ እንደታነፁና በአህመድ ግራኝ ወረራ ምክንያት ጠፍ ኾነው ቀርተው እንደነበር የሚያሳይ ሲኾን በሌላ በኩል ደግሞ ስማቸው እንኳ በአቡነ ሙሴ ገድል ተጠቅሶ አለመገኘቱ ነው፡፡

ምናልባት ከአህመድ ግራኝ ጦርነት በፊት ተገልጸው ከኾነ ከተሠወሩት መካከል ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ አለበለዚያ አቡነ ሙሴ ሳይኾን ሌላ ሰው አንጿቸው ሊኾን ይችላል፡፡ ቢኾንም ግን ለጊዜው ከዚኽ ትፊታዊ ምንጭ በስተቀር ሌሎች ምንጮችን ማግኘት አስቸጋሪ በመኾኑ አቡነ ሙሴ ሊያንጿቸው እንደሚችሉ ጠቁሞ ማለፉ ሳይሻል አይቀርም፡፡ ከዚያ በፊት ሳይሠወሩ ከ፲፮ኛው መ.ክ.ዘ ጀምሮ ጠፍተው እንደቆዩ ከወሰድንም የተሠወሩ ላንላቸው እንችላለን፡፡ ለኹሉም ግን የተሠወሩ የሚለው ጥልቅ ምርምርን ይጠይቃል፡፡ እዚኽ ላይ ለመነሻ የሚኾን ሐሳብ ከማስቀመጥ በዘለለ ከመሠረቱ አንጥሮ ለመጻፍ በዚህ ደረጃ አስቸጋሪ ይኾናል፡፡ የመጀመሪያው ነገር ገድሉ መጠናት ስለሚያስፈልገውና የአቡነ ሙሴ ታሪክም እጅግ እንቆቅልሽ ስለኾነ ነው፡፡ የዐዲስ አምባ ውቅር ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ግን በገድሉ ላይ በመገለጹ ብዙ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አቡነ ሙሴ አንፀው በሥውር ያልተውት ሕንፃ ነው፡፡ ስለ ገዳሙ ሥርዐት በገድላቸው ላይ የሚከተለውን ተገልጾ እናገኛለን፡፡

> *…ወበህየ አስተርአዮ እግዚእነ ክርስቶስ ለብፁዓዊ ሙሴ፡፡ ወወሀቦ ኪዳነ ወይቤሎ ዛቲ ምኔት ትኩን ለከ ከማሃ ለምኔተ አስቄጥስ ወመነኮሳቲሃኒ ይኩኑ ከመ ማኅበራኒሁ ለአቡነ [አባ] እንጦንስ፡፡ ወሥርዐታኒ ይኩን ከመ ሥርዐተ ገዳመ አስቄጥስ፡፡ . . . ኦ አኃው እለ ትነብሩ በዛቲ ምኔት ኢታብሑ አንስተ፤ ኢዘበቅል ወኢዘአድግ ዘእንበለ ተባእት፡፡ ወኢትግበሩ ንዋየ ለባሕቲትክሙ እንዘ ሀለውክሙ ውስተ ማኅበር፡፡ ወኢትፍልሱ እምሀገር ለሀገር፡፡*[35]
>
> [… በዚኽም ጌታችን (ኢየሱስ) ክርስቶስ ብፁዕ ለሚኾን ሙሴ ታየው፡፡ ይኽች ገዳም እንደ ገዳመ አስቄጥስ ትኹንልኽ፤ መነኰሳቷም እንደ አባ እንጦንስ ማኅበር፤ ሥርዐቷም እንደ አስቄጥስ ገዳም ይኹን ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት።

[35]ገድለ አቡነ ሙሴ፡ ቅጠል ፻፶፩፡፡

... በዚች ገዳም የምትኖሩ ወንድሞች ኸይ ሴትን አታስገቡ፤ ወንድ ካልኾነ በስተቀር የበቅሎም የአህያም ሴት አታስገቡ፤ በማኅበር ውስጥ እያላችሁ ገንዘብን ለግላችሁ አታድርጉ፤ ከሀገር ወደ ሀገርም አትዘዋወሩ፡፡]

ይኽ የሚያሳየው ገዳሙ የወንዶች መነኰሳት በአት ብቻ ይኾን ዘንድ ሥርዐት የወጣለት መኾኑን ነበር፡፡ ነገር ግን ከ፲፱፻፺ዎቹ ዐ.ም መጀመሪያ አካባቢ ገዳሙ በዐዲስ መልክ ሲቋቋም በሥርዐቱ ላይ ክርክር ነበር፡፡ ገድሉን መሠረት ያደረጉ (ይኽ ሐሳብ ገድሉ ለገዳሙ ሲጻፍ በሥርዋጽ የገባ ነው የሚሉም አሉ) መነኰሳት የወንዶች በኣት ብቻ እንዲኾን በማለት ሲከራከሩ ሌሎች ደግሞ ሴቶች መነኰሳይያትም ተፈቅዶላቸው የአንድነት ገዳም እንዲኾን በማለት ነበር፡፡ በእርግጥ ይኽ ጉዳይ ለዚኽ ገዳም ብቻ ዐዲስ ነገር አልነበረም፡፡ የወንዶች ብቻ ወይም የሴቶች ብቻ የኾኑ ገዳማት በሀገራችንም ኾነ በሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናት የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑ የወንዶችና የሴቶች ገዳም እንዲኾን በመወሰኑ ዛሬ የአንድነት ገዳም ኾኖ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

## ፫. የዋሻው ውስጥ የተለየዩ ክፍሎችና መገለጫዎቻቸው

የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ በተዘረጋ ዐለት ላይ የታነፁ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ነው፡፡ የእነዚኽ ክፍሎች ውጫዊ ገጽታዎቻቸው በአብዛኛው ዕድሳት የተደረገላቸው በመኾኑ ምን ዐይነት ኪነ ሕንፃዊ መገለጫ እንደ ነበራቸው ለመግለጽ ያስቸግራል፡፡ ዋሻዎቹ የተለያየ አገልግሎት ለመስጠት በሚያመች መልኩ የተከፋፈሉና የየራሳቸው መግቢያ እንዲኖራቸው ተደርገው የታነፁ ናቸው፡፡

ገዳሙ ወደ ስድስት የሚደርሱ ዋሻዎች ሲኖሩት የመጀመሪያውና በኪነ ሕንፃዊ ጥበቡ የተለየ ኾኖ መንፈሳዊ አገልግሎትን እየሰጠ የሚገኘው ትልቁ ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ከገዳሙ ግቢ እንደገባን ፊት ለፊት የምንመለከተው ነው፡፡ በቤተ መቅደስነት እያገለገለ መኾኑን የሚጠቁም ከዋሻው አናት ላይ የመስቀል ምልክት ያለው ጉልላት ተተክሎበታል፡፡ ሌሎቹ በዋናው የቤተ ክርስቲያኑ ክፍል በስተምዕራብና በስተምሥራቅ በኩል የሚገኙ ናቸው፡፡ የዋሻውን ምንነት በሚከተሉት አርእስት ሥር መመልከት እንችላለን፡፡



*ሥዕለ ብርሃን ፬. የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም፣ ከፊል ዕይታ*

## ፫.፩ ዋናው ዋሻ ቤተ ክርስቲያን (የመድኃኔ ዐለም ቤተ መቅደስ)

የገዳሙ ዋና ዋና መንፈሳዊ አገልግሎቶች የሚከናወኑበት ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ፎቅ ሲኾን የሚወጣውም በደረጃ ነው፡፡ ከሥሩም ለጸሎት ተብሎ የታነፀ ኹለት አዕማድ ያሉት፤ ለየት ያለ ኪነ ሕንፃዊ ጥበብ ያልታየበት የታች ቤት ይገኛል፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከመግባታችን በፊት ከሚገኘው ደረጃ በስተ ግራ በኩል መጠነኛ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ሲኖር በፊት ውኃ በማመንጨት ያገለግል ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ የወንዶች (በስተ ግራ)፣ የሴቶች (በስተ ቀኝ)ና የቅዳሴ መግቢያ (ፊት ለፊት የማይታይ በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ) ሦስት በሮች አሉት፡፡ የወንዶችን በር ተጠቅመን ስንገባ ከቅኔ ማኅሌቱ በፊት የሚገኝ አንድ መተላለፊያ እናገኛለን፡፡ ይኽን ዋሻ ልዩ የሚያደርጉትን ነገሮች ቀጥሎ በዝርዝር እናያለን፡፡

## ፫.፩ ጥንታዊ የጥበበ እድ ቅርስ *(An Ancient Handcraft)*

ወደ ቅኔ ማኅሌቱ ሲገቡ ቀድሞ ለዐይን ዕይታ የሚገባ የሰው ልጆች ፈጠራ የተገለጸበት ድንቅ የጥበበ እድ ውጤት ጣራው ላይ ተዘርግቶ እንመለከታለን። ይኸም ከቅኔ ማኅሌቱ ጣራ ላይ የተንጠለጠለ ዕድሜ ጠገብ ድባብ ነው። ይኽን ድባብ የጥበበ እድ ውጤት መኾኑ ሲገለጽ ዐዲስ ነገር ሊኾን እንደሚችል አስባለሁ። ድባቡ በወርቅ የተጌጠ ወይም ከጨርቅ መሰል ነገሮች የተሠራ አይደለም። እንዲኽ ከኾነ አስደናቂነቱ እምብዛም ሊኾን ይችላል። ምክንያቱም በወርቅ የተሸለሙ ለነገሥታትም (ወይም ለንግሥታት) ይኹን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ቆየት ያሉ ድባቦችን ጥቂት በማይባሉ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ማግኘት እንችላለን። ድባቡ በዐይነቱ እጅግ ለየት ያለ የሚያስብሉት ነገሮች የተሠራበት ቁስ፣ የአሠራር ጥበቡና በውስጡ የሚገኙ ጥንታውያን ሥዕላት ናቸው። ድባቡን ለመሥራት አገልግሎት ላይ የዋለው የዛፍ ልጥ ነው። በእጅ ጥበብ ሙያ በመታታት (ልጡን በማጠላለፍ) የተሠራ ነው።



*ሥዕለ ብርሃን ፳. ዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም የሚገኝ ከዛፍ ልጥ የተሠራ ጥንታዊ ድባብ*


የተሠራበትን ቁስ ስናነሣ በእርግጥም ልጥ መኾኑን በቀላሉ መለየት ይቻላል። አስቸጋሪ ሊኾን የሚችለው ልጡ ከምን ዐይነት ዛፍ እንደተወሰደ ለመለየት ስንሞክር ነው። ኾኖም ይኽ ድባብ ለብዙ ጊዜ መቆየት የቻለው ልጡ ጠንካራ ከኾነ የዛፍ ዐይነትና በቀላሉ ከማይነቅዝ እንጨት የተሠራ መኾኑን መረዳት ይቻላል። ስለዚኽ በአካባቢው

ልጣቸው ጠንካራ ከሚባሉት ዛፎች መካከል ዋና ዋናዎቹ አንቀባና ግራር ዛፍ ናቸው፡፡ ኹለቱም ዛፎች በተለይም ግራር በአካባቢው በስፋት የሚገኙ ናቸው፡፡ በመኾኑም ልጡ ከእነዚህ ዛፎች የአንዱን በመጠቀም የተሠራ ሊኾን ይችላል፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ የግራር ልጥ የተደራረበ ክፍል ስላለው ከድባቡ ዳርና ዳር አካባቢ ከሚታዩት ፍንጮች በመነሣት ከግራር ልጥ የተሠራ ሊኾን እንደሚችል ያመዝናል፡፡

የአሠራር ጥበቡም ትኩረትን የሚስብ ነው፡፡ በእጅ በመታታት የተሠራ ነው፡፡ ይኸም በአካባቢው ለተለያየ አገልግሎት የሚውለውን የዳውጃ[36] አሠራር ዕውቀት በመጠቀም የተሠራ ነው፡፡ ስለዚኽ ሌላ አጋዥ መሣሪያ ሳያስፈልገው በእጅ ብቻ የተከናወነ አካባቢያዊ ዕውቀትን የተላበሰ ነው፡፡ ከዚኽ የምንረዳው አካባቢው ያፈራቸውን ነገሮች በመጠቀም በእጅ ብቻ ድባብ ወይም ጃንጥላ መሥራት እንደሚቻል የሚያሳይ ሀገራዊ የጥበበ እድ ዕውቀት እንዳለ ነው፡፡ ድባቡ ከጣራው ላይ አግድም ከተዘረጋ ዕድሜ ጠገብ እንጨት ጋር በገመድ ታሥሮ ሳይንቀሳቀስ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ነው፡፡ ዛሬ ከምናውቀው የድባብ ዐይነት በአሠራሩና በተሠራበት ጥበብ በእጅጉ ልዩ ከመኾኑም ባሻገር እጀታ የለውም፡፡ ይኸም ተንቀሳቃሽ አለመኾኑን ያሳያል፡፡ ቅርጹን ስንመለከት ክብ ሲኾን ዙሪያውን በልጥ ገመድ በመደራረብ የታሠሩት እንጨቶች የድባብ ቅርጽ እንዲኖረው አድርገውታል፡፡

ይኽ ድባብ በጥንታዊ ሥዕላት ያሸበረቀ ነው፡፡ የድባቡን ጫፍ ይዘው ዙሪያውን የተሣሉት የቅዱሳን ሥዕላት እንዲሁም ዙሪያውን ለጌጥነት የተቀመጡት መሥመሮችና የመስቀል ምልክቶች የጥንቱን ጥበብ በሩቁ እንድንሳለመውና ለዚያ ዘመን ልዩ አድናቆት እንድንቸረው ያደርጋሉ፡፡ ሥዕላቱ ከአፈርና ከዕፅዋት ቅጠል በተቀመሙ ቀለሞች (ቀይ፣ ጥቁር፣ ነጭና አረንጓዴማ ቀለሞች) የተሣሉ ናቸው፡፡ ጎላ ጎላ ያሉ ዐይኖችና አክሊለ ብርሃን አላቸው፡፡ ይኸም ቅዱሳንን እንደሚወክሉ ያሳያል፡፡ የድባቡ ውስጣዊ ክፍል በነጭ ቀለም የተቀባ ሲኾን ሥዕላቱ የተሣሉት የድባቡን የጠርዝ ዙሪያ በመከተል ነው፡፡ መካከለኛው ክፍል በአብዛኛው በተለያዩ መሥመሮች እንዲሁም በመስቀለኛ ቅርጾች የተዋበ ነው፡፡ ሥዕላቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፲፪ውን ቤተሰቦች የሚወክሉ ናቸው፡፡ በግልጽ ከሚታዩት ሥዕላት መካከል ሐዋርያ የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል፡፡ ይኸም የቅዱሳኑን ስም ለመለየት ከተጻፉት ቃላት መካከል ሳይጠፋ የቀረው ነው፡፡ በጥቅሉ ከሥዕላቱ መካከል በድባቡ በአንዱ ገጽ ብቻ ለአብነት የቀሩ አምስት ሥዕላትን በአግባቡ መለየት ይቻላል፡፡ ሌሎች የጠፉና እየጠፉ ያሉ ናቸው፡፡ ከድባቡ ማእከላዊ ክፍል ላይ ዐይኖቹ አካባቢ ብቻ ይታያሉ፡፡ ምናልባትም ይኽ ሥዕል የጌታችን ሳይኾን አይቀርም፡፡ ሐዋርያትና ሌሎች ቅዱሳን ደግሞ ዙሪያውን ከበው እንደተሣሉ ያሳያል፡፡

[36] ዳውጃ ከተፈተለ የዛፍ ልጥ (ልጥ ከእርጥብ ግንድ ቅርፊት ውስጣዊ ክፍል በመላጥ የሚገኝ ለስለስ ያለ ክፍል ነው) በእጅ የሚሠራ በገጠሩ አካባቢ ለሥጥ ማስጫ አንዳንድ ጊዜም ለመኝታነት የሚያገለግል ነው፡፡



*ሥዕለ ብርሃን ፯. የድባቡ ውስጣዊ ዕይታ*

እነዚኽ ቅዱሳት ሥዕላት ቀለማቸው እየለቀቀና የጃንጥላው ጌጣጌጦችም በጊዜ ብዛት እየረገፉ ትውልድ ሳያውቃቸው ሊጠፉ መኾናቸውን ለሚመለከት ጥልቅ ኀዘንን ይፈጥራል፡፡ የድባቡን ውጫዊ ክፍል ባለው ኹኔታ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቀለም የተቀባ እንደነበር አመላካች ነገሮች አልፎ አልፎ ቢታዩም አንድም የሥዕል ምልክት አልተገኘም፡፡ በርግጥ ውስጣዊ ክፍሉን በሥዕላት እንዳስጌጡት ውጫዊውንም በተመሳሳይ ኹኔት ሳያስጌጡት አይቀርም፡፡ በሌላ በኩልም በድባቡ ውስጣዊ ክፍል ፲፰ውን ቅዱሳን ኹሉ ለመሣል ስለማያስችል ውጫዊው የድባቡ ክፍል ሥዕላት ተሥለውበት እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ይኽ ድባብ በአቡነ ሙሴ ጊዜ እንደተሠራና ከጊዜ ብዛት የተነሣ እየደበዘዘ መምጣቱ እንጂ ብርሃን ይሰጥ እንደ ነበር ሊቃውንቱ ይናገራሉ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስም አገልግሎት እየሰጠ ያለ ጥንታዊ ቅርስ ነው፡፡ በአጠቃላይ በየትኛውም አካባቢ ሊገኝ የማይችል የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን ብቸኛው ቅርስ ነው ብሎ ማለፍ ይቻላል፡፡

## ፫.፩.፪ የውስጣዊ ክፍሎች ዕቅድ (Internal Plans and Divisions)

የቤተ ክርስቲያኑ ውስጣዊ ክፍሎች ከውጭ ወደ ውስጥ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት፣ ግብዐተ መንጦላእት[37] እና መቅደስ ናቸው። ቅኔ ማኅሌቱ ከኹሉም በመጠኑ ሰፋ ያለ ሲኾን የቅድስቱንና የመቅደሱን ሕንፃ ቅርጽ ተከትሎ የታነፀ ነው። ይኽ ክፍል የክብነት ቅርጽ ያለው ሲኾን ዙሪያውን በመዞር መመልከት ይቻላል። ወደ ምሥራቅ በኩል እየጠበበ ይሔዳል። በስተ ምዕራብ በኩል ያለው ክፍል የማኅሌት አገልግሎት የሚሠጥበት ነው። በዚኽ ክፍል አጽሞችን የያዙ ከዐለቱ በታች የሚገኙ መቃብራት ይገኛሉ። እነዚኽም ቅርብ ጊዜ ባይኾንም ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ የተቆፈሩ ናቸው። የተወሰኑት መቃብራት ተከፍተውና አጽሞቹ ተሰባስበው በትልልቅ የእንጨት ሳጥኖች በማከማቸት በስተ ምሥራቅ በኩል በክብር ተቀምጠዋል። በቅኔ ማኅሌቱ በስተ ምሥራቅ በኩል ለብዙ ጊዜ ሲያገለግል የነበረ እጅግ ግዙፍ የኾነ የእንጨት መንበር ተቀምጦ ይታያል።

ቅድስቱና መቅደሱ በአንድ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ይህ ሕንፃ በዐራቱም ገጾቹ የታነፀ በመኾኑ ሙሉ ወጥ ልንለው እንችላለን። ይኽ ኹኔታም ዋሻውን በሀገራችን ከሚገኙ በርካታ የዋሻ አብያተ ክርስቲያናት ለየት እንዲል ያደርገዋል። ምክንያቱም ከዋሻ ውስጥ ተፈልፍሎ የሚገኝ ሙሉወጥ ሕንፃ የተለመደ ባለመኾኑ ነው። ያልተለያየው ከጣራውና ከመሠረቱ በኩል ብቻ ነው። ዙሪያውን በመዞር መመልከት ይቻላል። ይህ ሕንፃ የዋሻውን ማእከላዊ ክፍል ይይዛል። ይኽ የአሠራር ሥልት የሐናፅያኑን ጥበብ እንድንመረምር ያደርገናል። በዋሻ ውስጥ ሙሉ ወጥ አድርገው ማነፃቸው በጊዜው ሙሉ ወጥ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናትን የመሥራት ዕውቀቱ እንደነበር ያሳያል። ነገር ግን ሙሉ ወጥ አድርገው ካነፁት አይቀር ለምን ጣራው ላይ ያለውን የዐለቱን ክፍል ሙሉ በሙሉ አላስወገዱትም? የሚል ጥያቄ ሊፈጠር ይችላል። ይኽን ያላደረጉበት በዋናነት የዐለቱን ባሕርይ በመረዳታቸው ነው። ምክንያቱም ዐለቱ ጠንካራ ዐለት አይደለም። በቀላሉ በዝናብና በፀሐይ ሐሩር ሊጎዳና ቤተ ክርስቲያኑን ለአደጋ ሊያጋልጠው የሚችል ነበር። ስለዚኽም የላይኛው የዐለት ክፍል ሳይነካ መቅረቱ በውስጥ ላሉት የዋሻው ክፍሎች መከላከያ እንዲኾናቸው ታስቦ ነው። በአብዛኛው በመቄት የሚገኙ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ባህላቸው ዋሻ ተኮር መኾኑ ለዚኽ ነው። ስለዚህ ከዐለት የሚታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ ወጥ ወይም ዋሻ ተኮር የሚኾኑት የዐለቱ ዐይነት ስለሚወስናቸው ነው። ሐናፅያኑ ሙሉ ወጥ ሕንፃ ለማነፅ ቢፈልጉም ዐለቱ ጠንካራ ካልኾነ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ለማነፅ ይገደዳሉ።

[37]ግብዐተ መንጦላእት በቤተ መቅደሱና በቅድስቱ መካከል የሚገኝ ቦታ ሲኾን በአብዛኛው የተለመደው በውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነው። ይኽም ወደ ቤተ መቅደስ መዳረሻ በመኾኑ ከካህናት በስተቀር ሌላ ሰው አይገባበትም።

የሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን አሠራር ሥርዐት የሚያወሱ ወደ ቅደስቱ የሚያስገቡ ሦስት በሮች በሰሜን፣ በደቡብና በምዕራብ በኩል ይገኛሉ፡፡ ዕድሜ ጠገብ በኾኑ የእንጨት ሳንቃዎች የተገጠሙ ናቸው፡፡ ቅድስቱ ከግብዐተ መንጦላእቱ በኹለት ዐምዶች የተከፈለ ነበር፡፡ ነገር ግን ኹለቱን ዐምዶች በግንብ በማገናኘት ወደ መቅደሱ የሚያስገቡ በሮች በዐዲስ መልክ ተሠርተዋል፡፡ ግብዐተ መንጦላእቱ ደግሞ ከመቅደሱ በሌሎች ኹለት ዐምዶችና በመጋረጃ ተለይቷል፡፡ ኹለቱም ክፍሎች ሥርዐተ ቅዳሴ የሚከናወንባቸው ሲኾኑ ካህን ካልኾነ በስተቀር ማንኛውም ሰው መግባት አይችልም፡፡

## ፫.፩.፫ ኪነ ሕንፃ (Architecture)

የዚኽ ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና የኪነ ሕንፃ መገለጫዎች የበር አሠራር ቅርጾች፣ የግድግዳ ላይ ቋሚ መሥመሮች፣ ዐምዶች፣ ጉልላትና የጣራ ላይ ንድፎች ናቸው፡፡ የኹሉም በሮች ቅርጻቸው ዐራት ማዕዘን ነው (ሥዕለ ብርሃን ፳ን ተመልከት)፡፡ ምንም እንኳን የአኵስማውያን የበር አሠራር ኪን ባይኖራቸውም በብዙ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚንጸባረቅ በዐራት ማዕዘን ቅርጽ ገባ ብሎ የማነፅ ሥልትን የተከተለ ነው፡፡ በተለይም በላሊበላ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት የዚህ ዐይነት ሥልት ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ወደ ቤተ አማኑኤል ግቢ መግቢያ ያለውን በር መመልከት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ብዙዎቹ የመቄት ወረዳ ውቁራት ሕንፃዎች የዚኽ ዐይነት የበር ቅርጽ አላቸው፡፡

በቅድስቱ ምዕራባዊ የሕንፃው ክፍል ማለትም ከመግቢያ በሩ አናት ላይ በግራና በቀኝ በኩል ኹለት በመስቀል ቅርጽ የተቀረጹ ክፍት መስኮቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚኽም ሕንፃው ለመንፈሳዊ አገልግሎት የታነፀ ስለመኾኑ አስረጂ ናቸው፡፡ አምሳያቸው በላሊበላ በተለይም ቤተ ማርያም ሕንፃ ላይ ጎልተው ይታያሉ፡፡ ዐምዶቹን ስንመለከት በኹለት ጎኖቻቸው ብቻ የቅስት ቅርጽ ያላቸው ናቸው፡፡ መቀነቻ የላቸውም፡፡ ቅስታቸውም እጅግ የተለጠጠ ወይም የተዘረጋ ነው፡፡ የእነዚኽ ዐይነት ዐምዶች በሌሎች አካባቢዎች የተለመዱ አይመስለኝም፡፡ በሀገራችን የሚገኘው የዐምድ አሠራር ሥልት ልዩ ልዩ መኾኑን ያንጸባርቃሉ፡፡ ከቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ ወደታች የተቀረጹ መሥመሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚኽም ለግድግዳው ውበት ተብለው የታነፁ ናቸው፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን



*ሥዕል ብርሃን ፯ (በስተግራ). መስቀለኛ መስኮቶች፣ በስተምዕራብ ወደ ቅድስቱ ከሚያስገባው በር አናት ግራና ቀኝ*



*ሥዕል ብርሃን ፰ (በስተቀኝ). ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚገኙ ዐምዶች በከፊል (በስተግራ የሚታየው መንበር ነው)*

ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ሌላው ዋና የኪነ ሕንፃ መገለጫ ኾኖ የሚጠቀሰው ጣራው ላይ የተቀረጸው ጉልላት ነው፡፡ ከጣራው ወደ ላይ ገባ ያለና ክብ ኾኖ የታነፀ ነው፡፡ የዚኽ ዐይነት ጉልላት በብዙ ቦታዎች በተለይም በመቄት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ያኽልም ዋሻ ሚካኤል (መቄት)፣ አቡነ አሮን (መቄት)፣ ጠፉ ቤተ ክርስቲያን[38] (ጋይንት)ና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከጉልላቱ አጠገብም አንድ የመስቀል ቅርጽ ይገኛል፡፡ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ አንድ ተኩል ሜትር ቁመት ያለው ጠባብ ጎሬ አለ፡፡ ይኽም በችግር ጊዜ ታቦቱ ተሸሽጎበት የነበረ እንደኾነ ይነገራል፡፡

## ፫.፩.፬ የዋሻው ጥንታዊ ሥዕላት (Ancient Paintings)

ጥንታዊ ሥዕላት በገዳሙ ከሚገኙት መገለጫዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚኽም ከድባቡ ውስጥና ግድግዳ ላይ የተሣሉ ናቸው፡፡ የድባቡ ሥዕላት ከሞላ ጎደል ከላይ ተመልክተዋል፡፡ የዋሻው የግድግዳ ላይ ሥዕላት የሚገኙት ከቅኔ ማኅሌቱ ፊት ለፊት ማለትም ከቅድስቱ ግድግዳ ምዕራባዊ ገጽ ላይ ነው፡፡ ከምዕራብ በኩል ከሚገኘው በር ላይም እንዲኹ ሥዕላት ይታያሉ፡፡ እነዚኽ ሥዕላት በዐይን እምብዛም አይታዩም፡፡ ይኽም ከጊዜ ብዛት የተነሣ እየደበዘዙ ስለመጡ ነው፡፡ ምናልባትም በዐይን ሊታዩ የሚችሉ ከኹለት የማይበልጡ ሥዕላት ናቸው፡፡ በሥዕለ ብርሃን በተገኘው መረጃ መሠረት ድባቡ ላይ ከሚገኙት ሥዕላት ጋር በአሣሣል ሥልታቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ዐይኖቻቸው ጎላ ጎላ ተደርገው የተሣሉ ሲኾኑ ቀይና ጥቁር ቀለም በመጠቀም ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ሥዕላቱ ጥንታዊ የአሣሣል ሥልትን የሚከተሉ ናቸው፡፡ ምናልባትም

[38] ይኽ ውቅር ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ጠፍ (አገልግሎት የማይሰጥ በመኾኑ ጠፍ ይሉታል) ተብሎ የሚታወቅ ሲኾን አገልግሎት እየሰጠ ያለ አይደለም፡፡ ይኽም ከግራኝ አሕመድ ወረራ ጀምሮ ነው (Tsegaye 2014, p. 76)፡፡

ከጎንደር ዘመን በፊት የተሣሉ መኾን አለባቸው፡፡ ሥዕላቱ የሚወክሉትን ቅዱስ መለየት አስቸጋሪ ነው፡፡




*ሥዕለ ብርሃን (፲፱፣ ፳). ከገዳሙ ዋሻ ውስጥ የሚገኙ የግድግዳ ላይ ሥዕላት*

እነዚኽ ሥዕላት (የጃን ጥላውንም ጭምር) በአቡነ ሙሴ በዐራተኛው መ.ክ.ዘ. እንደተሣሉ በአካባቢው በትውፊት መልክ የሚነገር ታሪክ አለ፡፡ በርግጥ ይኽ ትክክል ሊኾን እንደሚችል ፈርጆ ማለፉ አስቸጋሪ ነው፡፡ የእነዚኽ ዐይነት ሥዕላት በሌሎች የአቡነ ሙሴ ሕንፃዎች አለመኖራቸው አጠያያቂ ነው፡፡ ድባቡን ያሠሩት አቡነ ሙሴ እንደኾኑ የሚነገረው በገድላቸው ውስጥ መጠቀስ ነበረበት፡፡ ሥዕላትን በዚኽ ዐይነት ድባብ ውስጥ መሣል ደግሞ እጅግ ያልተለመደ ነው፡፡ ድባቡ በአካባቢው ምእመናን ረዳትነት ካልኾነም ከእርሳቸው በኋላ የአካባቢው ሰዎች በሚያውቁት የእጅ ጥበብ መሠረት የተሠራ ሊኾን ስለሚችል ሥዕላቱም በኋላ ጊዜ የተሣሉ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ ጥልቅ ጥናትን የሚጠይቅ ቢኾንም የግድግዳውና የድባቡ ሥዕላት በተመሳሳይ ጊዜ የተሣሉ ይመስላሉ፡፡ የአሣሣል ሥልታቸውም ተመሳሳይ ነው፡፡

የኾነ ኾኖ ሥዕላቱ በአቡነ ሙሴ ጊዜ ባይኾንም እንኳ እጅግ የቆዩ ሊኾኑ እንደሚችሉ ያሳያሉ፡፡ ምናልባት በአንዳንድ የአቡነ ሙሴ አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ በቤተ ሐራ ኢየሱስና በዝጆ ማርያም ዋሻ አብያተ ክርስቲያናት[39] ጉልላታቸው ላይ የደበዘዙ ቀለሞች ይታያሉ፡፡ ምናልባት ተመሳሳይ ሥዕላት ተሥሎባቸው የነበሩ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳ ከዐዲስ አምባ መድኃኔ ዐለም ሥዕላት ጋር በተጠቀሙባቸው ቀለማትም ይኹን በአሣሣል ሥልታቸው የተለዩ ቢኾኑም የድባ መቅደሰ ማርያም ኹሉም አብያተ መቃድስ

[39]እነዚኽ የዋሻ አብያተ ክርስቲያናት በመቄት የሚገኙ ሲኾኑ በአቡነ ሙሴ እንደታነፁ ይነገርላቸዋል (Tsegaye 2014)፡፡

በሥዕላት ያጌጡ ናቸው፡፡ የድባ መቅደሰ ማርያም ያሉት ሥዕላት በ፲፯ኛው መ.ክ.ዘ. የተሣሉ መኾናቸው ተገልጿል፡፡[40] ዐዲስ አምባ ያሉት ግን ጊዜውን ለማወቅ አስቸጋሪ ቢኾንም ቀደም ብለው የተሣሉ ሳይኾኑ አይቀርም፡፡

## ፫.፬ ሌሎች የዋሻው ክፍሎች

ከዋናው ዋሻ ቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ በኩል የየራሳቸው መግቢያ ያላቸው ሦስት ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚኽ ውስጥ አንዱ በቅርብ ጊዜ የቅድስት አርሴማ ቤተ መቅደስ እንዲኾን ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ውስጣዊ ዕቅዳቸውንና ኪነ ሕንፃዊ መገለጫዎቻቸውን ስንመለከት የተሠሩበት ዐላማ ለንብረት ማስቀመጫ፣ ለእንግዳ መቀበያ (ማረፊያ)ና ለጸሎት አገልግሎቶች ብቻ እንደኾነ ነው፡፡ ዛሬ የቅድስት አርሴማ ቤተ መቅደስ የኾነው ኹለት ክፍሎች ያሉት ሲኾን አሠራሩ ለንብረት ማስቀመጫ በሚያመች መልኩ ነው፡፡ ይኽም ከግድግዳው መሐል ላይ ሰው በሚደርስበት መልኩ ለመጻሕፍትና ለሌሎች ንብረቶች ማስቀመጫ ይኾን ዘንድ ታስቦ የተሠራው ደረጃ ማሳያ ነው፡፡

በሌላኛው የዚኽ ክፍል ቅስት የሌላቸው ኹለት ዐምዶች ሲኖሩ የታነፁትም ክፍሉን ከኹለት ለመክፈል ሳይኾን ለድጋፍ ሰጭነት ብቻ ነው፡፡ ከዕቅዳቸው በተጨማሪም ለቤተ መቅደስነት የተሠሩ መኾናቸውን የሚጠቁም ለምሳሌ የመስቀል ወይም የጉልላት ምልክት የላቸውም፡፡ ሌላኛው ክፍል የተሠራለት ዐላማ እንደተጠበቀ ኾኖ እስካኹንም ድረስ የንብረት ወይም የንዋየ ቅዱሳት ማስቀመጫ ነው፡፡ ሌሎች ክፍሎችም እንዲኹ ለጸሎትና ለማረፊያነት የሚያገለግሉ አሉ፡፡ በስተ ምሥራቅ መጨረሻ በኩል የምናገኘው ቤተ ልሔም ሲኾን ይኽም አገልግሎቱን እየሰጠ ያለ ክፍል ነው፡፡

# ፬. ማጠቃለያና የጥቆማ ሐሳቦች

## ፬.፩ ማጠቃለያ

ይኽ ጥናት ከአካባቢው ውጭ እምብዛም የማይታወቀውን የዐዲስ አምባ ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም ለማስተዋወቅ ተሞክሮበታል፡፡ ዋሻውም ኹለት ተራራዎች መካከል የሚገኝ ሲኾን ለብዙ ዘመናት ከምሁራን ዕይታ ውጭ ኾኖ የቆየ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በአቡነ ሙሴ እንደታነፀ ይነገርለታል፡፡ አቡነ ሙሴም በጵጵስና ስሙ አቡነ ሚናስ ተብሎ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ኹለተኛው ጳጳስ ነው፡፡ በትውልድ እስራኤላዊ ሲኾን

[40] Witakowska, E. B. (2014). YäAmba Maryam. In: Alessandro Bausi (ed.), *Encyclopedia Aethiopica,* Vol. 5. Harrassowitz Verlag, Wiesbaden. p. 3.

በምንኩስናም የአባ መቃርስ ልጅ ነው። ይኽ ዋሻ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ክፍሎች ያሉት ሲኾን ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ኹኔታዎቹ የሚገኙት በመድኃኔ ዐለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው።

ሙሉ ወጥነት ያለው ቤተ መቅደሱንና ቅድስቱን በአንድ ላይ የሚይዘው ሕንፃ በዋሻው ውስጥ ታንፆ መገኘቱ ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱና ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ይኽ በዋሻ አብያተ ክርስቲያናት የተለመደ ገጽታ አይደለም። በሥዕላት ያሸበረቀ የአካባቢው የጥበበ እድ ውጤት የኾነ ጥንታዊ ድባብ መገኘቱ ሌላው ልዩ መገለጫው ነው። ይኽ ድባብ ያልተለመደ የሚያደርገው ከዛፍ ልጥ በተፈተለ ገመድ መሰል ነገር በእጅ በመታታት የተሠራ መኾኑ ነው። ከዋሻው ምዕራባዊ የቅድስቱ ግድግዳ ላይና ከድባቡ ውስጥ የተሣሉት ሥዕላት ጥንታዊነት የሚታይባቸው ናቸው። ዐይኖቻቸው ጎላ ብለው መሣላቸው ዋነኛ መገለጫቸው ነው። እነዚኽ ሥዕላት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደበዘዙና እየጠፉ ያሉ ናቸው።

## ፬.፪ የጥቆማ ሐሳቦች

ይኽ ጥናት ቤተ ክርስቲያኑ ከዚኽ ቀደም ካለመታወቁ አንጻር ያሉትን ገጽታዎችና ታሪኩንም በዐጭሩ ለመግለጽ የተሞከረበት ቢኾንም ያልተገለጹ በረካታ ጉዳዮች አሉ። ዋሻው መቼና በማን እንደታናፀ በግልጽ ለማወቅ ተጨማሪ ጥናቶች እጅግ ወሳኝ ናቸው። በተለይም የአቡነ ሙሴ ታሪክ ጉዳይ በምሁራን ዘንድ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ስለዚኽ ከዚኽ በተጨማሪ ጠለቅ ያለ የምርምር ሥራ ሊሠራበት እንደሚችል ተስፋ ይደረጋል። አቡነ ሙሴ መሠወሩን ወይም ማረፉን ለማወቅ የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ቢመለከቱት የተሻለ ነው። እንዳነፃቸው የሚነገርላቸው ሌሎች ውቁራት አብያተ ክርስቲያናትም እንዲኹ በጥናቱ መስክ ተከታታይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው። ከዚኽም ሌላ አቡነ ሙሴ በገድሉ እንደተገለጸው በተለያዩ ቦታዎች ብዙ ያልተከሰቱ ውቁራት አብያተ ክርስቲያናት እንዳነፀ ስለሚገልጽ ይኽም ሌላ የቤት ሥራ ይኾናል። እየደበዘዙና እየጠፉ የሚገኙትን የዋሻውን ሥዕላት የሚመለከታቸው ባለሙያዎች በጥናት የተመሠረተ እንክብካቤ ሊያደርጉላቸው የሚገባ መኾኑን ይኽ ጥናት ያመላክታል። ከዚኽ በተጨማሪ ይኽን ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢውን ኅብረተ ሰብእ ተጠቃሚ ለማድረግ የመስህብነት አገልግሎት እንዲጀመር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚኽም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ሊሠራ ይገባዋል። የአካባቢው ኅብረተ ሰብእ እንዲጠቀምም ኾነ ቤተ ክርስቲያኑ ለጉብኝት ምቹ እንዲኾን ቢያንስ የጥርጊያ መንገድ ሊኖረው ይገባል።